ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 30 ታህሳስ 03/2018 ዓ.ም

## በውስጥ ገፆች

የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 20ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በደማቅ ሁኔታ
ገጽ 1

5.6 ቢሊዮን ብር ጉዳት በማድረስ የተጠረጠሩ ከፍተኛ አመራሮች በከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰሱ
ገጽ2

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት 43 የውጭ ዜጎች ሰነድ በማጭበርበር ተጠያቂ ማድረጉን ገለጸ
ገጽ 5

**የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት NCRS ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!**

## "ሌብነትን እንጠየፍ፣ "

"በታሪክ ተወቃሽ እንዳንሆን ኢትዮጵያውያን ቀልብ ገዝተን ሰላማችንን እናፅና፣ በንግግር እንመን፣ በተሰማራንበት የሥራ መስክ ሁሉ በትጋት እንሥራ፣ ሌብነትን እንጠየፍ፣ የሀገር ጥቅም እና የሕዝቦቻችንን ክብር እናስቀድም፣ ለዘመናዊነት እና ለውጥ ክፍት እንሁን፣ ሉዓላዊነታችንን በሁሉም መስክ እናሳካ!" - ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



## በሲቭል ስርቪስ ማሻሻያ መሠረት የሚያርፈድና ከስራ የሚቀር ሰራተኛ ከደሞዙ እንዲቆረጥ ይደረጋል ብሏል።

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ ይህን ያሉት የሶስት ወር የስራ ክንውን ሪፖርት ለህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት የሰው ሃብት ልማት ስራ ሰምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበበት ወቅት ነው።

በዚህም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ የሰራተኛ ምዘናን አስመልክቶ ማብራሪያ የሰጠ ሲሆን ሰራተኞቹን ለመመዘን የሚያስችል 144 ሺህ አከባቢ ጥያቄዎች መዘጋጀታቸውን ገልጿል።

ሰራተኛው የሚመዝነው በሁለት ነገር መሆኑን ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ ገልፆ 1ኛው ባህሪ ሚዘና ሲሆን 2ኛው ደግሞ የተማረው ትምህርት ያንን ስራ ያሰራል ወይ የሚለውን ለማረጋገጥ የስራ ዘርፍ ምዘና ይመዘናል ብሏል።

በዚህ ተመዝኖ ከሚጠበቀው ዝቅተኛ ውጤት የሚያመጣ ከሆነ ስልጠና ይሰጣል ብሏል። በተደጋጋሚ ስልጠና ወስደው ማለፍ ያልቻለ ከስራ ይባረራል እንዲሁም ይህንን ፈተና አልፈተንም ያለ የመንግስት ሰራተኛም ከስራ ይባረራል ብሏል።

ለዚህም ሁለቱም አካላት ማለትም መንግስትም ወጪ አውጥቶ ሰራተኛ መድቦ ስልጠና መስጠት አለበት ፣

## የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 20ኛውን የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በደማቅ ሁኔታ አከበረ





የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በኮሚሽኑ አዳራሽ የ20ኛውን የኢትዮጵያ ብሔሮች ፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በውይይትና ወዳጅነት በተሞላበት መልኩ አከበረ። በዓሉን"በዲሞክራሲያዊ መግባባት ለህብረ-ብሄራዊ አንድነት' በሚል መሪ ቃል ተከብሯል።

በበአል መድረኩ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ(ፒ.ኤች.ዲ) በመገኘት ለተሰብሳቢው የእንኳን አደረሳችሁ መልክት አስተላልፈዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የበለፀገች መሆኗን ጠቅሰው፣ ይህን ብዝሀነት በመቻቻልና በእኩልነት መርህ በመጠቀም ህብረ-ብሄራዊ አንድነታችንን ማጠንከር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የስነምግባር ግንባታ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ በበኩላቸው ሀገራችን ባለብዙ አይነት ባህል፣ ቋንቋና ሃይማኖት ያላት ሀገር መሆኗን በማስታወስ፣ በኮሚሽኑ ውስጥ ብዝሀነትን ያማከለ አስተሳሰብና ተግባር መኖር እንዳለበት አስረድተዋል። ሁሉም ሰራተኞች የሚመጡበትን ብሄረሰብ ባማከለ መልኩ ችሎታቸውንና ታማኝነታቸውን መሰረት በማድረግ በጋራ በመሥራት ሀገርን የተሻለ ማድረግ እንደሚቻል ከተወያዩ በኋላ አንድነትን በተግባር ማሳየት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በፕሮግራሙ የተለያዩ ብሄረሰቦችን የሚወክሉ ባህላዊ አልባሳት ለብሰው የኮሚሽኑ ሰራተኞች በአሉን አክብረዋል።

ይህ ዝግጅት በኮሚሽኑ ውስጥ ያለውን የህብረ-ብሄራዊ መግባባትና አንድነት የበለጠ ለማጠንከር ያለመ መሆኑ ተገልጿል።

ከዚህ መድረክ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አዳራሽ ዓለም አቀፉን የነጭ ሪባን ቀን በውይይት አክብሯል።

በፕሮግራሙ የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ በበዓሉ ንግግር አድርገዋል።

የነጭ ሪባን ቀንን በማስመልከት የመወያያ ሰነድ የኮሚሽኑ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ስልጠና ክፍል ሀላፊ ወ/ሮ ኮከብ አንበርብር ከታሪካዊ ዳራው በመነሳት አቅርበዋል።

# 5.6 ቢሊዮን ብር ጉዳት በማድረስ የተጠረጠሩ ከፍተኛ አመራሮች በከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰሱ

የግዥ መመሪያና ውሳኔዎችን በመጣስ የጥራት ችግር የታየበት የአፈር ማዳበሪያን ግዥ በመፈጸም፣ እንዲሁም ማዳበሪያውን ከውል ውጭ በሆነ መንገድ በማጓጓዝ በመንግሥት ላይ ከ5.6 ቢሊዮን ብር በላይ ጉዳት በማድረስ የተጠረጠሩ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች ማዳበሪያው የጥራት ችግር ያለበት መሆኑን እያወቁ ወደ አገር እንዲገባ በመተባባር በተጠረጠሩ ሠራተኞች ላይ ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቷል።




የፍትሕ ሚኒስቴር ዓቃቤ ሕግ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ የከባድ ሙስና ወንጀሎች ችሎት የቀረበው ክስ እንደሚያስረዳው፣ ተጠርጣሪዎቹ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1 ሀ)፣ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 9(1 ሀ እና 2) የተደነገገውን በመተላለፍ በሥልጣን አላግባብ በመገልገል የሙስና ወንጀል መፈጸማቸው ይገልጻል።

ዓቃቤ ሕግ ክሱን የመሠረተው በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ሰባት አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች፣ በኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ፣ በአንድ የግብርና ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራርና በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት ሁለት ከፍተኛ አመራሮች ላይ ነው።

በወንጀሉ ተጠርጥረው በሕግ ቁጥጥር ሥር የዋሉትና ክስ የቀረበባቸው የኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን አመራሮች መካከል በክስ መዝገቡ በአንደኛ ደረጃ የተጠቀሱት የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የነበሩት አቶ ክፍሌ ወ/ማሪያም ጋዎ ናቸው።

በተጨማሪም በኮርፖሬሽን የግብርና ግብዓት ምርትና አቅርቦት አብይ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚና የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ ሰብሳቢ በነበሩት አቶ ወልደአብ ደምሴ ክብረት፣ የኮርፖሬት ሀብት አመራር ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚና የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ አባል በነበሩት አቶ ተሳይ ሜጫ ወልደ ስላሴ፣ የኮርፖሬት ፋይናስ ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የኮርፖሬሽኑ የግዥ ኮሚቴ አባል በነበሩት ሃይለማሪያ ነጋሳ፣ በኮርፖሬሽኑ ከፍተኛ የግዥ ባልደረባና የማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ አባልና ፀሐፊ በነበሩት አቶ ሚሊዮን ገረመው እሸቱ፣ በኮርፖሬሽኑ የግብርና ምርት ማሳደጊያዎች አቅርቦት ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚና የኮርፖሬሽኑ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ አባል እንዲሁም የብሔራዊ አፈር ማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ ፀሐፊ በነበሩት አቶ ሰለሞን ገብሬ መላክ እና በኮርፖሬሽኑ የግብዓት ግዥና ትራንዚት ክፍል ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ዘላለም ዳኘ ሮሪሳ እንደ ቀደም ተከተላቸው ተጠርጥረው ተከሰዋል።

ከኮርፖሬሽኑ ውጭ በወንጀሉ ተሳትፈዋል ተብለው ከተጠረጠሩት መካከል በኢትዮጵያ ግብርና ሚኒስቴር የግብዓት አቅርቦት መሪ ሥራ አስፈፃሚና የብሔራዊ አፈር ማዳበሪያ ግዥ ቴክኒካል ኮሚቴ ሰብሳቢ በነበሩት አቶ መንግስቱ ተስፋ ላቀ፣ የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ምክትል ሥራ አስፈፃሚ የነበሩት ካፒቴን ወንደሰን ካሳ አሰፋ፣ በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ፀጋዬ በርሃ ኪዳኑና በኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት የጅቡቲ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አለባቸው ሞልቶት ዳኜ ናቸው።

ዓቃቤ ሕግ የክሱን ምክንያት ሲያብራራ፣ ተከሳሾች የመንግስት የሥራ ኃላፊነት ላይ ተመድበው ይሰሩ በነበረበት ወቅት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት በማሰብ የ2017/2018 የምርት ዘመን የአፈር የማዳበሪያ ግዥን፣ በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የፀደቀ የግዥ መመሪያ፣ በገንዘብ ሚኒስቴር በተዘጋጀው የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት፣ አቅርቦትና ግዥ መመሪያ 977/2016ን፣ ኮርፖሬሽኑ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ድርጅት፣ ከብሔራዊ የክልል መንግስታት እና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የፈፀመውን የአምስትዮሽ ውል፣ ኮርፖሬሽኑ ከኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድረጅት ጋር በህዳር 2017 ዓ.ም የተፈራረመውን የአገልግሎት አሰጣጥ ውል፣ ከብሔራዊ ክልል መንግስታት በኮርፖሬሽኑ የአፈር ማዳበሪያ እንዲያስመጣ በተሰጠው ውክልና እና የኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የ2017/2018 የአለምዓቀፍ የአፈር ማዳበሪያ ግዥን መፈፀምና ማስፈፀም ሲገባቸው ኃላፊነታቸውን ያለአግባብ በመገልገል ከላይ በተጠቀሱት የህግ ማዕቀፎችና ውሎች የተዘረጋውን የዓለምዓቀፍ የአፈር ማዳበሪያ የግዥ ሥርዓትን እና የቦርዱን ውሳኔ በግልፅ የወንጀል ድርጊታቸው ሆን ብለው ጥሰዋል የሚል ነው።

በኢትዮጵያ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ውስጥ የማዳበሪያ ግዥ ኮሚቴ አባል የሆኑት ተጠርጣሪዎች የኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ 2017/2018 ምርት ዘመን ቀሪ የዳፕና የዩሪያ የአፈር ማዳበሪያ ግዥን በተመለከተ፣ "እስካሁን የማዳበሪያ አቅርቦት በውላቸው መሠረት አሚልተው ለኮርፖሬሽኑ ያቀረቡ ድርጅቶች ተመርጠው በውስን ጨረታ እንዲፈፀም" የሚል ውሳኔ ያሳለፈ ቢሆንም፣ ቦርዱ ውሳኔውን ከሰጠበት ሚያዚያ 21 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት ከኮርፖሬሽኑ ጋር ውል ያልነበረውን፣ በቦርዱ ውሳኔ መሠረት በጨረታው ለመሳተፍ የተቀመጠውን መስፈርት የማያሟላውን፣ ከቀረበው የጨረታ ሰነድ ጋር ለማዳበሪያው ከአምራቹ የሚሰጥ የጥራት ምርመራ ሰርተፍኬት ወይም አምራቹ ለሚያቀርበው ማዳበሪያ ሊሰጥ የሚገባውን የጥራት ማረጋገጫ ያላቀረበውን፣ ተጠርጣሪዎቹ አስቀድመው በስውር ለተመሳጠሩበት ሚድ ገልፍ ኢንተርናሽናል ልሚትድ

ወደ ገጽ 3 የዞረ

# 22ኛው የዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን

የዘንድሮው ዓለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን «ትውልድን በሥነ ምግባር፣ ተቋማትን በአሰራር» በሚል መሪ ቃል በፌዴራልና በክልሎች ተከብሯል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የመዝጊያ ፕሮግራም የአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በተለመደው መልኩ በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል። 22ኛው መሪ ቃል «ትውልድን በሥነ ምግባር፣ ተቋማትን በአሰራር») ትኩረት ያደረገ ነበር።

በሀገር አቀፍ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን መሪነት በፌዴራልና በክልሎች የተለያዩ መድረኮች ተካሂደዋል።

ወጣቶች የሙስና መንስኤም ሆነ መፍትሄ መሆናቸውን፣ ሥነ ምግባራዊ ትውልድ መገንባት የሙስናን ሥር የሚነቀል መሆኑን አፅንኦት የሰጠው የዘንድሮው የአለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀን በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች፣ የፀረ ሙስና ክለቦች አባላት፣ የመንግሥት ተቋማት ተወካዮች፣ የሲቪክ፣ ህዝባዊ ድርጅቶች፣ ማኅበራት እና ሌሎችም አካላት በስፋት ተሳትፈዋል።

በተለያዩ ክልሎች በክልል ደረጃ የፀረ ሙስና ኮሚሽኖች የተለያዩ ፓናል ውይይቶች፣ የወጣቶች መድረኮች፣ የሥነ ጥበብ ትርኢቶችና የማኅበረሰብ ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ተካሂደዋል።

## ከስነምግባር ባፈነገጠ መልኩ የለበሱ ተጠርጣሪዎች በህግ ቁጥጥር ስር ዋሉ - የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ከሀገራችን ባህልና ሥነ-ምግባር ያፈነገጠ አስነዋሪ አለባበስ ለብሰው በአደባባይ እና በቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት ለሕዝብ የታዩ ተጠርጣሪዎችን ላይ ምርመራ መጀመሩን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው 3ኛው የG-Power TikTok Creative Award ላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ባህልና መልካም ሥነ-ምግባር ተቃራኒ በሆነ መልኩ ሰውነታቸውን የሚያጋልጥ አስነዋሪ አለባበስ ለብሰው በአደባባይና በቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት ለሕዝብ የታዩ ተጠርጣሪዎችን ከነግብረ-አበሮቻቸው በቁጥጥር ሥር አውሎ ምርመራ መጀመሩን አስታውቋል።ፖሊስ በዝግጅቱ ላይ ተሳታፊ ወይም አዘጋጅ ሆነው የተጠረጠሩትን የሚከተሉት ግለሰቦች ጠቅሷል።

ወንጌላዊት ገብረ እንድርያስ በርሄ፣ በርከት ፀጋዬ ጅፋር፣ መቅድም ደረጀ መንግስቱ፣ ግሩም ገዛሀኝ ቀጭኔ እና

ዮሃንስ መኮንን ሀ/ማርየም ናቸው።የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ፣ ከህብረተሰቡ ባህልና እሴት ያፈነገጡ አለባበሶችና መጤ ባህሎች ተስፋፍተው በትውልድ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያስከትሉ በማሰብ፣ ተጠርጣሪዎቹ ላይ የሕግ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የጀመረውን ምርመራ እንደሚያጠናክር ገልጿል።




### ከገጽ 2 የዞረ

ለተባለው ድርጅት ዝቅተኛ ዋጋ አቅርቧል በማለት 102 ሺህ ሜትሪክ ቶን ዩሪያ ማዳበሪያ ከቻይና ቲንጂያን ወደብ እንዲያቀርብ መርጠው የጨረታ ውጤቱ ለብሔራዊ የማዳበሪያ ግዥ የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲላክ መወሰናቸውን ክሱ ያብራራል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቦርዱ ለውስን ጨረታውን ያስቀመጠው ቅድመ ሁኔታ መሟላቱን በማረጋገጥ ለብሔራዊ የማዳበሪያ ግዥ የቴክኒክ ኮሚቴ የጨረታ ውጤቱን መላክ ሲገባው፣ ይህንን ኃላፊነት አለመውጣቱንም አቃቤ ህግ በዝርዝር ባቀረበው ክስ ላይ ገልጿል።

በአጠቃላይ ተከሳሾቹ የቦርዱን ውሳኔዎች፣ የግዥ መመሪያና የውል ድንጋጌዎችን በመጣስ ግዥ እንዲፈፀም ማድረጋቸውን የአቃቤ ህግ ክስ ማብራራቱን ሪፖርተር ጋዜጣ በትላትናው እትሙ አስነብቧል።

በዚህም የተጋገረ ማዳበሪያ ማካካሻ 204 ሺህ ዶላር መክፈሉን፣ ከመቀሌ መርከብ ላይ ጊር በመነቀሉ 100 ሺህ ዶላር ወጪ መደረጉን፣ ለማዳበሪያ ግዥ 39,992,860 ዶላር መከፈሉንና በድምሩ 40,296,860 ዶላር ወይም 5,681,857,260 ብር በህዝብና በመንግስት ላይ ጉዳት መድረሱን አቃቤ ህግ በክሱ በዝርዝር አስቀምጧል።

ተጠርጣሪዎቹ ባደረሱት ጉዳት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተሳታፊ በመሆናቸው ስልጣናቸውን አላግባብ ተጠቅመዋል በማለት አቃቤ ህግ የከባድ ሙስና ወንጀል ክስ መስርቶባቸዋል።

### ከገጽ 1 የዞረ

ሰራተኛውም ለተልዕኮ ራሱን ማዘጋጀት አለበት ብሏል።

ይህ ምዘና ሰራተኛውን ለመቀነስ ሳይሆን ለተቋማት ተልዕኮ ለማዘጋጀት ዓላማ ያለው እና ክፍተትን ማዕከል ያደረገ ስልጠና በመስጠት ሰራተኛን ለማብቃት እንደሆነ አብራርተዋል። የስልጠናው ፕሮግራም በሚንስትሮች ምክር ቤት ተወስኖ ስርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶለታል ብሏል።

አምስት ተቋማት ማለትም አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ ሲቭል ስርቪስ ዩንቨርስቲ ፣ ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት እና የአፍርካ ልህቀት አካዳሚ የባህሪ ብቃት መገንባት የሚያስችሉ 125 ሞጁሎችን በማዘጋጀት ለስልጠና ዝግጁ

ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION
1993
ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission
ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች
EARS

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1
NCRS

## ርዕሰ -አንቀፅ

### ሀሰተኛ ሰነድ መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት በመገንዘብ ልንከላከለው ይገባል!

ሀሰተኛ ሰነድ (የተፈጠረ ወይም የተሻሻለ ሰነድ) መጠቀም የሙስና ወንጀል ሲሆን፣ በህግ፣ በገንዘብ፣ በማህበረሰብ እና በግለሰብ ደረጃ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል:: እነዚህን ጉዳቶች በዝርዝር እንመልከታቸው:-የህግ መዘዝ (Legal Consequences)በኢትዮጵያ ህግ መሰረት፡ የሙስና ወንጀለኛ አዋጅ 881/2007 እንደ ወንጀል ይቆጥረዋል፣ቅጣቱ፡ እስከ አስራ አምስት (15) ዓመት እስራት ወይም ከፍተኛ ቅጣት፣ለምሳሌ:- የሀሰተኛ መታወቂያ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የመንጃ ፈቃድ፣ የባንክ ደብተር፣ የመሬት ሰነድ መጠቀምና የመሳሰሉትን ይህን ቅጣት ያስከትላል:: በውጭ አገርም ተመሳሳይ ከባድ ቅጣት አለ (ለምሳሌ በአሜሪካ በስራ-ትያስቀጣል)::የገንዘብ ጉዳትለግለሰብ፡ ቅጣት መክፈል፣ የተወሰደ ገንዘብ መመለስ፣ የስራ መጥፋት፣ለባንክ/ድርጅት፡ ሚሊዮኖች ብር ኪሳራ (ለምሳሌ የሀሰተኛ ቼክ በመጠቀም ገንዘብ መሰረቅ)፣ለመንግስት፡ የግብር ማጣት፣ የፓስፖርት/ቪዛ ስርዓት መበላሸት::

የማህበረሰብ እና የተቋም ጉዳትበህብረተሰቡ ውስጥ የእምነት ቀውስ ይፈጠራል:: ሰዎች ሰነድ ሲያዩ እንኳን ይጠራጠራሉ፣የመንግስት ተቋማት (ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ባንኮች) ተግባር ይስተጓጎላል፣የሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ በመጠቀም ያልተገባ ሰው ስራ ሲያገኝ የሌሎች ብቃት ያላቸው ሰዎች መብት ይገፋል::የግለሰብ ህይወት ላይ የሚያስከትለው ጉዳትየስም መጥፋት፡ አንዴ ተይዞ ሀሰተኛ ተብሎ ቢፈታም ህብረተሰቡ ለዘላለም ይጠራጠራል፣የስራ መጥፋት፡ አብዛኛው ድርጅት የሀሰተኛ ሰነድ መጠቀምን ሲያውቅ ወዲያውኑ ያባርራል፣የቤተሰብ መበታተን፡ እስራት ሲመጣ ሚስት/ባል፣ ልጆች ይሰቃያሉ፣የስነ-ልቦና ቀውስ፡ ሁልጊዜ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ የተጋለጥኩ እንደሆነ ስሜት::በሌሎች ላይ የሚያስከትለው ቀጥተኛ ጉዳትየሀሰተኛ የመሬት ሰነድ በመጠቀም ንብረት መውረስ ባለቤቱ ይቸገራል፣የሀሰተኛ የህክምና ፈቃድ በመጠቀም ህመምተኛ መጉዳት ወይም መሞት፣የሀሰተኛ ፓስፖርት በመጠቀም ሽብርተኝነት፣ ሰው ማዘዋወር፣ የመድሃኒት አዘዋዋሪነት መፈጸም::በኢትዮጵያ በሀሰተኛ ሰነድየመገልገል ወንጀል በተደጋጋሚ የሚታይ ሲሆን ይህም የመንግስት ተቋማትን እምነት እየሸረሸረ ይገኛል::

በተለይም የሀሰተኛ መታወቂያ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ፣ ፓስፖርትና መንጃ ፈቃድ ማዘጋጀት የመንግስት ገቢን የሚቀንስ፣ የሽብርተኝነት የሚያስፋፋና የህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት እየሸረሸረ ይገኛል::በተጨማሪም፣ የሀገር የደህንነት፣ የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ቀውስ እያስከተለ ይገኛል::በሀሰተኛ ሰነድ የመገልገል ወንጀልን ለመቀነስ መንግስት ዘመናዊ የዲጂታል ሲስተም (እንደ ብሄራዊ መታወቂያ፣ ዲጂታል የመሬት ምዝገባ ስርዓት፣ ኤሌክትሮኒክ የትምህርት ማስረጃ የማረጋገጥ) ስራ በተሟላ መተግበር፣ የህግ ማስከበር ስራን ማጠንከር (ከፍተኛ ቅጣት መጣልና ቀልጣፋ የፍርድ ዉሳኔ)፣ የህዝብ ግንዛቤ ማሳደግ (በተለያዩ የሚዲያ አማራጮች፡በቲቪ፣ ሬዲዮ፣ በትምህርት ተቋማት) እና የተቋማት ቅንጅታዊ አሠራር (ፖሊስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር ወ.ዘ.ተ) ማጠንከር አስፈላጊ ነው:: ከዲጅታል አሠራር ጋር በተገናኘ ተቋማት ተግባራዊ እያደረጉ ቢገኝም በፍጥነት ተደራሽ መሆን ይጠይቃል:: በተጨማሪም በህጋዊ ሰነድ የመስጠት አገልግሎት ላይ ያለውን ቢሮክራሲያዊ መሰናክሎች በመቀነስና የአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፈና በማሳደግ ዜጎች ወደ ህገ-ወጥ መንገድ እንዳይሄዱ መከላከል ይቻላል:: እነዚህ ተግባራት በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ ከተደረጉ በሀገር ደረጃ ያለውን በሀሰተኛ ሰነድ የመገልገል ወንጀልን መቀነስ ስለሚቻል ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን እናድርግ የሚል መልዕክት እናስተላልፋለን::

# ከሙስና የፀዳና በቅንነት የሚያገለግል አመራር ለክልሉ ሁለንተናዊ ለውጥ ወሳኝ ነው ተባለ

የጋምቤላ ክልል ርዕሠ መስተዳድር ክብርት ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድ "አመራሩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በመፀየፍ ለህዝቡ ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት አርአያ ሊሆን ይገባል ብለዋል::
ሁሉም የህዝብ አገልጋይ አመራር በወንበር ላይ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን የህዝብን አደራ ተቀብሎ በታማኝነት ማገልገል ነው:: ስለሆነም በየደረጃው የሚገኝ አመራርና ፈጻሚ ሙስናን በተግባር መፀየፍ፣ ስልጣንን ለግል ጥቅም ማዋል የህዝብን ሀብት መዝረፍ ብቻ ሳይሆን የነገውን ትውልድ ተስፋ ማጨለም መሆኑን በመረዳት፣ ከማንኛውም የሙስና ተግባር ራሱን ማራቅ አለበት:: አርአያነት ያለው ተግባር፣ አመራሩ በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር ንጽህናውን በማሳየት ለሠራተኛውና ለህዝቡ አርአያ የሚሆን የሞራል ልዕልና ሊኖረው ይገባል፣ ቀልጣፋና ቅን አገልግሎት:- የህዝብን እንግልት በማስቀረት፣ አድልዎ የሌለበት፣ ፈጣንና ውጤታማ አገልግሎት መስጠት የዜግነትና የመንግስት ኃላፊነት ግዴታ መሆኑን መቀበል አለበት፣ የህግ የበላይነትን ማክበር የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድሙ፣ ለህግና ለስርዓት የሚገዙ እንዲሁም ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ አሰራሮችን መከተል ይገባል::
ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ ብልሹ አሰራር የዕድገታችን እንቅፋት ነው ፤ የክልሉን ሰላምና ልማት ለማረጋገጥ በጋራ እንታገለው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል::




## በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት አራት ወራት በ29 ተቋማት በተደረገ ክትትልና ድጋፍ 43.9 ሚሊየን ብር ወደ መንግስት ትሬዠሪ ተመላሽ ማድረግ መቻሉን ተገለጸ

የአዲስ አበባ ፋይናንስ ቢሮ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት የማህበራዊ ዘርፍ ቡድን መሪወ/ሮ አለም ታደገ እንደተናገሩት ፋይናንስ ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 84/2016 ከተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መካከል በጀት የመደልደል እና የደለደለው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋል አለመዋሉን ማረጋገጥ እንደመሆኑ በ2018 በጀት ዓመት ባለፉት አራት ወራት በ29 ተቋማት ባደረግነው ክትትልና ድጋፍ አላግባብ ወጪ የተደረገ 43.9 ሚሊየን ብር ወደ መንግስት ትሬዠሪ ተመላሽ ተደርጓል ብለዋል::
ወ/ሮ አለም አያይዘውም ተቋማት የተበጀተላቸው በጀት በአግባቡ ስራ ላይ እንዳይውል የሚከለክላቸው የአሰራር ችግር እንደሌለ የገለጹት ወ/ሮ አለም ችግር አለ ከተባለ ከአፈፃፀም አንፃር የሚፈጠር ችግር በመሆኑ እንደ ፋይናንስ ቢሮ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙ ግኝቶች ውይይት እንዲያደርጉ በማድረግ እና ችግርን የለየ ስልጠና በመስጠት የሃብት ብክነትን ለመቀነስ እንሰራለን ብለዋል::
በመጨረሻም ከተማችን በምታመነጨው ገቢ የምትተዳደር እንደመሆኗ ይህን ውስን ሃብት በግልጽነትና በተጠያቂነት መርህ ለመተግበር የሚመለከተው ሁሉ ኃላፊነቱን እንዲወጣ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል::

## የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድን ጨምሮ በተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ስም ሃሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጅ የነበረዉ ግለሰብ በቁጥጥር ስር ዋለ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው ቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጅ የነበረዉ ግለሰብ ተይዞ ክስ እንደተመሰረተበት ፖሊስ አስታውቋል::
ዳንኤል ሀይለጊዮርጊስ የተባለው ግለሰብ የተለያዩ ሀሰተኛ ሰነዶችን እንደሚያዘጋጅ ከህብረተሰቡ የተሰጠውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ በተደረገ የክትትልና የመረጃ ሥራ በተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ስም የተዘጋጁ ሀሰተኛ ሰነዶች ተገኝተዋል::
በኦሮሚያ ንግድ ቢሮ፣ የብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት የሚገልፅ ማህተም፣ በሲ.ፒ.ዩ የቢዝነስ እና ቴክኖሎጂ ኢንፎርሜሽን ኮሌጅ ማስረጃ ፣ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ፣የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሰነድ፣የንግድ ስራ ፍቃድ፣ የወሳኝ ኩነት ሰነዶችና በልዩ ልዩ ተቋማት ስም የተዘጋጁ ደብዳቤዎች ተገኝተዋል::
ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማዘጋጀት የሚገለገልባቸው 3 ፕሪንተሮች፣ላፕቶፕ እና የተለያየ አይነት ያላቸው ወረቀቶች በኤግዚቢትነት የተያዙ ሲሆን በግለሰቡ ላይ ተገቢውን ምርመራ በማጣራት ክስ መመስረቱን የፒያሳ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ አስታውቋል::
ሀሰተኛ ሰነድ አዘጋጅቶ በመሸጥና ገዝቶ በመጠቀም በአቋራጭ ጥቅም ለማግኘት ጥረት የሚያደርጉ አካላትን ህብረተሰቡ ሲመለከት ለፀጥታ አካላት በማሳወቅ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው እያደረገ ያለውን አስተዋፅኦ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ መልእክቱን አስተላልፏዋል::

## የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት 43 የውጭ ዜጎች ሰነድ በማጭበርበር ተጠያቂ ማድረጉን ገለጸ

የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት 43 የውጭ ዜጎች ሰነድ በማጭበርበር እና በዜግነት ጉዳይ ተጠርጥረው ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል ሲል አስታውቋል::
ይህ የተባለው የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ሰላማዊት ዳዊት፣ የተቋሙን የ2018 ዓ.ም ሩብ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ለውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረቡበት ወቅት ነው::
በዚህም በሀሰተኛ ሰነድ የቪዛና የፓስፖርት አገልግሎት ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ እየበዛ ነው ብለው፣ በሀሰተኛ ሰነድ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት የማግኘት ሙከራን የማጣራትና በድርጊቱ የተሳተፉትን በቁጥጥር ስር የማዋል ስራ እየሰራ ነው ብለዋል::
በመሆኑም በተያዘው በጀት ዓመት ሩብ ዓመት 43 የውጭ ዜጎች ሰነድ በማጭበርበር እና በዜግነት ጉዳይ ተጠርጥረው ተጠያቂ እንዲሆኑ ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል::
በተጨማሪም በሀሰተኛ ሰነድ አገልግሎት ለማግኘት የሚደረግን ማጭበርበር ለማስቀረት ቴክኖሎጂን የመጠቀም ስራ እየተሰራ ነው::

## በስህተት ወደ አካውቱ የገባን ብር የመለሰው መልካም ወጣት

በስህተት ወደ አካውንቱ የገባውን 400 ሺህ ብር ለባለቤቱ የመለሰው መልካም ወጣት፣ በወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ዕውቅና ተሰጠው::
በአማራ ክልላዊ መንግሥት ደቡብ ወሎ ዞን መቅደላ ወረዳ የሚኖር ወጣት ሰይድ አሊ፣ በስም መመሳሰል ምክንያት ከአቶ ሚኪያስ አየለ የተላለፈለትን 400 ሺህ ብር ለባለቤቱ በመመለስ፣ ከወረዳው ፖሊስ ጽ/ቤት ዕውቅናና ምስጋና ተችሮታል:: ወጣቱ፣ ብሩ እንደተላለፈለት አቶ ሚኪያስ ደውሎ በስህተት ብር ማስገባቱን በነገረኝ ሰዓት ያለምንም ማመንታት ወዲያውኑ ብሩን መልሶታል ብሏል::
የመቅደላ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ ኢንስፔክተር ጌታየ ቢራራ እንደገለጹት፣ ሰዎች ለገንዘብ ብለው ሰው እየገደሉ በሚገኝበት ዘመን፣ በአካውንት የገባን ገንዘብ በቅንነትና በታማኝነት መመለስ ትልቅ ሰውነትን የሚጠይቅና ለሌሎችም አርአያ የሚሆን ተግባር በመሆኑ፣ ወጣቱ ለሰራው በጎ ተግባር በተቋሙ ስም ምስጋናቸውን አቅርበዋል::
የመቅደላ ወረዳ ኮሙኒኬሽን መረጃውን ባገኘነው መሰረት የወጣቱ መልካም ተግባር የሌሎቸም ወጣቶች ተምሳሌት የሚሆን ተግባር ነው::



## የፈረንሳይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀድሞው ፕሬዝዳንት ሳርኮዚ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጸደቀ

የፈረንሳይ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀድሞው ፕሬዝዳንት ኒኮላስ ሳርኮዚ በ2012 የድጋሚ ምርጫ ዘመቻቸውን ለማካሄድ ህገ-ወጥ የገንዘብ ድጋፍን እንደተጠቀሙ የተወሰነባቸውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽድቋል፡፡


ይህ ውሳኔ በሌላ የክስ መዝገብ ይግባኝ እስኪሉ ድረስ ከእስር በተለቀቁ በሁለት ሳምንት ጊዜ ዉስጥ የተሰማ ለታሪካቸው እና ለዝናቸው ተጨማሪ ሽንፈት ሆኗል፡፡

ሳርኮዚ፤ በ2007 አሸናፊ በሆኑበት የፈረንሳይ ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ ወቅት ከሊቢያ ሚስጥራዊ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ሴራ ጠንስሰዋል በሚል ጥፋተኛ ከተባሉ በኋላ በፓሪስ ላ ሳንቴ ወህኒ ቤት ለ20 ቀናት ታስረው ቆይተዋል፡፡

ሳርኮዚ በበኩላቸው ምንም አይነት ጥፋት አለመፈጸማቸውን በመግለጽ ክሱን አስተባብለዋል፡፡

የሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ÷ሳርኮዚ ባልተሳካው የምርጫ ዘመቻቸዉ ወቅት በማጭበርበር ከመጠን በላይ ወጪ በማውጣታቸው የተላለፈባቸውን የአንድ ዓመት እስራት ግማሹ በይቅርታ የሚታለፍ ሲሆን፤ የመጨረሻ እና የማይቀየር አድርጎታል፡፡

በፈረንሳይ ህግ መሰረት÷ይህ የእስራት ቅጣት በእግር ላይ በሚታሰር የኤሌክትሮኒክስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ወይም በዳኞች በሚወሰኑ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች ክትትል እየተደረገበት በቤት ውስጥ ሊፈጸም ይችላል ተብሏል፡፡



## ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

### በሙስና የተከሰሰ ግለሰብ በ12 ዓመት ጽኑ እስራት ተቀጣ

በሙስና ወንጀል የተከሰሰው በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የማኦ ወረዳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ሀላፊ የነበሩት አቶ ቀጤሳ ፈዬራ ዴሳ በ12 ዓመት ፅኑ እስራት እና በ4,451 / አራት ሺ አራት መቶ ሀምሳ አንድ / ብር የገንዘብ መቀጮ ተቀጣ፡፡

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ ቁጥር 3 እና 23/2ሀ/ስር የተደነገገውን በመተላለፍ፤ አንቀፅ ቁጥር 23/2ሀ/ ከአንቀፅ ቁጥር 1ሀ ጋር አብሮ ተከሳሽ የተከሰሰው አቶ ቀጤሳ ፈዬራ ዴሳ የማኦ ኮሞ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ከቤ/ጉ/ክ/ መንግስት የቆላማ አካባቢዎች ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት የተቀበለውን የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ገንዘብ በሀሰተኛ ውክልና ሰነድና በሀሰተኛ ድርጅት በመፍጠር በፍርድ ቤት ክስ በመመስረት በድምሩ 4,995,659.45 ብር በራሱ አካውንት እንዲገባ በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ያገኘ በመሆኑ በከፍተኛ የሙስና ወንጀል ተከሷል፡፡የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዐቃቤ ህግ የቀረበውን ክስ ተቀብሎ ከመርመር በኋላ ተከሳሹን በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ብሎ ያገኘ ሲሆን፤ ህዳር 15 ቀን 2018 ዓ/ም በዋለው የወንጀል ችሎት ተከሳሹን በ12 ዓመት ፅኑ እስራት እና በ4,451 /አራት ሺ አራት መቶ ሀምሳ አንድ/ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

## ሀሰተኛ የውጭ ሀገራት ገንዘቦችን ይዘው ሲቀሳቀሱ የነበሩ ተጠርጣሪዎች ተያዙ-

ሀሰተኛ የውጭ ሀገራት ገንዘቦችን ይዘው ሲቀሳቀሱ የነበሩ 4 ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ እያጣራ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ገልጧል፡፡

ተጠርጣሪዎቹ በርዋ ከበደ፣ ሙላት አባይ፣ ሳሙኤል ሙሉጌታ እና ጃኮ ፔንዞ የተባሉ ሲሆን፣ የወንጀል ድርጊቱን የፈጸሙት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 አካባቢ ነው፡፡

ሙላት አባይ የተባለው ተጠርጣሪ የተበደረውን ገንዘብ ልመልስልህ በማለት ሀሰተኛ መቶ ዶላር ለጓደኛው ሰጥቷል፡፡ ጓደኛውም ያንን ዶላር ወደ ባንክ ይዞ ለመመንዘር ሲሞክር ሀሰተኛ መሆኑ ተረጋግጦ ለፖሊስ ጥቆማ ሰጥቷል፡፡

ፖሊስ ጥቆማውን መነሻ በማድረግ በወንጀሉ ውስጥ ዋና ተሳታፊ የሆነውን





ከነአባሪው በመያዝ በሰራው የአካል ፍተሻ 1000 ሀሰተኛ ዩሮ አግኝቷል፡፡ በተጨማሪም ምርመራውን በማስፋት ሳሙኤል ሙሉጌታ የተባለው ተጠርጣሪ ሀሰተኛ ገንዘቡን እንደሰጣቸው መረጃ ሲሰጥ ይህንን ግለሰብ በቁጥጥር ስር ሲውል በእርሱ ላይ 1400 ሀሰተኛ ዶላር ተገኝቷል፡፡

ሶስተኛው ተጠርጣሪ ሀሰተኛ ዶላሩን ከየት እንዳመጣው ሲጠየቅ የውጭ ሀገር ዜጋ ወደሆነው ጃኮ ፔንዞ መምራቱን ተከትሎ፣ ይህ አራተኛ ተጠርጣሪም በመገናኛ አካባቢ 5600 ሀሰተኛ ዶላር ይዞ ሲንቀሳቀስ በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

በአጠቃላይ ከተጠርጣሪዎቹ ከ8,000 በላይ ሀሰተኛ የውጭ ሀገር ገንዘብ ተይዞ ምርመራው እየተካሄደ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ህብረተሰቡን ሀሰተኛ ገንዘብ ከመቀበልና ከማስፋፋት እንዲቆጠብ፣ አጠራጣሪ

የዘንድሮው 22ኛው የፀረ ሙስና ቀን መሪቃል

**ትውልድን በሥነምግባር፤ተቋምን በአሰራር !**

# ኪነ-ጥበብ

## መሻት

ሁልግዜ መመኘት ፡
ምንም አያደርግም የሰውን መቃኘት ፡፡
የራስህን ፈልግ የሌላ አይጠቅምም ፡
ለፍተህ ጥረህ ግረህ ይቺ አለም ባትሞላም፡፡
በስጋ ፍላጎት ብተፍጨረጨርም ፡
የሰውን መመኘት ምንም ትርፍ የለውም ፡፡
ኪሳራ ሳይመጣ ትርፍህን እንደያዝክ ፡
ከሀገር ከምድርህ ሙስናን አጥፈተህ ፡፡
በስነ ምግባርህ ሀገርህን መርተህ ፡
ለልጅ ለጆችህም ግብረገብ አውረሰህ ፡፡
በስነ ምግባርም አይምሮን አንጸህ ፡
ለትለወዱ ፍሬ በለሷን መግበህ ፡፡
ከአልባሌ ንዋይ ከማጥ ውስጥ አውጥተህ ፡
ሙስና ሌብነት እነዲጠፋ ታግለህ ፡፡
መብራቱን አብርተህ በሙያህ ተጠበህ ፡
ውሀውንም ለቀህ እንዲሁ አድርገህ ፡፡
አንተ ግን በስራህ ሁል ጊዜ ሙስና ፡
እስከመቼ ድረስ ልትኖር በልመና ፡፡
እራስህ ጠንክረህ ሌሎቹንም አጽና ፡
ሙስና የሚሰራ ጠንቅ ስላለበት ፡፡
አንዴ እግር ጥሎት ወኀከኒ ጥለውት ፡
ልጆቹን በትኖ ሜዳ ላይ ሲዋተት፡፡
አንድ ቀን አይቀርም በስራህ መቀጣት ፡
ስነ ስርአቱን ለትውልድ አድርሱ ፡፡
የአዋቂውን ምግባር በክፉ እነዳይወርሱ ፡
ትውልዱን ታደገው ግባ ወደ አዲሱ ፡፡
ቶሎ ተመልሰው በፍቅር ይንገሱ ፡
ሁል ጊዜ በፍቅር አንተን ሲከተሉ ፡፡
አንተ ግን ከምግባር መጥፎን እንዲጥሉ ፡
አስተዋጽኦ አርገህ ውሀውን ከጥሩ ፡፡
ይሉ ነበር ድሮ አባቶች በተረት ፡
አሁን ግን ትውልዱ እንዳይንከራተት ፡፡
ግዴታ አለብህ ብልሃቱን መስጠት ፡
ሙስና ክፉ ነው ሕየወትን ያስታል ፡፡
ከዚያም ስትመለስ በስህተትህ መሐል ፡
ፀፀት እንዳይጎዳ ከኪስህ አውጥተህ ፡፡
መልሶ ያገር ሃብት እንዳይገባ ኪስህ ፡
የአገርህ ግበር ካንተው ተገብሮ ፡፡
በሙስና ባህሪ ካዝናው ተበርበሮ ፡
አደራ ያን አይተህ አንዳትተላለፍ ፡፡
ቅንነት ብቻ ነው ወንድሜ ያንተ ትርፍ ፡፡
ቅንነት ብቻ ነው እህቴ ያንቺ ትርፍ ፡
ተመለስ የሰው ልጅ ወደ ተፈጥሮህ ፡፡
በለሷን ስትበላ ከገነት ወጣህ ፡
አሁን እንደገና ይሔ ሙስናህ ፡፡
ከስነ ምግባርህ እነዳያወጣህ ፡

// በአስቴር መኮንን//
ከውሃና ኢነርጂ ዘርፍ

# መልካም ሥነምግባር የህሊና እርካታ ነው!